# የኣዞ ዕንባ (ከትንቢተ እሣያስ)

በዓሣዬ

የፋሺሥቱን ቅሪት በሆዳቸው ሸምቼ
ባዕዳንን ኣምላኪ የእሣትን ዕራፊ
ቆሻሻ  ቡቱቱዎች  ከሥሬ  ጎዝጉዤ
ለጫማዬ  ድልዳል ብርሃኑን ደርቤ
ምቾቱ ሲደላኝ ሙቀቱ ሲሰማኝ ከኣንጀቴ ኣምጬ
የዓዞ ኩል ዕንባየን ከዓይኔ ጨምቄ
በንፍጥ ሥነፋረቅ በሣግ ተናንቄ ፡
ዝርግፍግፍ ኣረኩት ለኺያ ትምክህተኛ
ዳግም ከእጄ ስትወድቅ ታይታኝ  ኢትዮጵያ ።

ወይ ቅሌት ! ወይ መዓልቲ !

ኣያት ቅድመ ኣያቶች ጀግና ኣባቶቻችን
የባንዳ ኣባቱን ጌታ ዱቼ ሞሶሎኒን
ጠራርጎ ከኢትዮጵያ በውርደት ማባረሩን
ማሥታወሥ ቢሣነው መች እወቅሰዋለሁ
የማሰብ ጭንቅላቱን ካንሰር ሥለፋቀው ።

ዛሬም ጀግኖች ኣሉን እንደ ኣሸን የፈሉ
ለተገንጣይ ባንዳ ገሃነም የሆኑ ፡
በኣራቱም ማዕዘናት ሞት ሞት ሲሸታችሁ
የኣህያ ባል ከጅብ ተረቱን እረሥታችሁ
ከላይ ታች ዘጭ መረጭ ከንቱ ድካማችሁ
ምንም ኣያዋጣም ደርሷል ፍፃሜኣችሁ !።

ድል ለኢትዮጵያ !

02/02/2015 G C.